4ኛ ተከሳሽ በመስከረም 2008 ዓ.ም ቀኑ ባልታወቀ በኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ዞን ቡራዩ ከተማ በተከበረ የኢሬቻ በአል የአከባቢውን ወጣቶች በማግኘት መንግስት የአዲስ አበባ እና የኦሮሚያን የተቀናጀ ማስተር ፕላን ሊያፀድቅ ስለሆነ ተደራጅተን ይህን መንግስት እስከ ህይወት መስዋትነት መክፈል አለብን ከስልጣን እናስወግዳለን በማለት የአመጽ ጥሪ በማስተላለፍ ተሳታፊ ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሾች የአነግን የሽብር ተልእኮ ተግባራዊ ለማድረግ በፖለቲካ ፓርቲ ሽፋን ስም በህቡዕ በመደራጀትና በኢሮሚያ ክልል አመጽ እንዲነሳ በተለይም በፊንፊኔ ዙሪያ፣ በቡራዩ ከተማ ወጣቶች ለአመጽ በኋይል እንዲነሱ በአከባቢው ባለስልጣናት ላይ እና በመንግስት ተቋማት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በመሳተፋው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በአነግ የሽብር ቡድን ውስጥ በማናቸውም መልኩ መሳተፍ ወንጀል ተከሰዋል፡፡

ብርሀኑ ወ/አገኝ
የፌዴራል ረዳት ጠቅላይ ዐ/ህግ

የማስረጃ ዝርዝር

<u>ለ/ የሰነድ ማስረጃ</u>

1. ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብሄራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት በቀን 23/9/08 በቁጥር ደመ42/47/08 1ኛ ተከሳሽ በሞባይል ስልክ መስመር ቁጥር 0911195897 እና 0911406968 ሲደርጋቸው የነበሩ የስልክ ግንኙነቶች በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/01 አንቀፅ 14/1/ መሰረት የተሰበሰበ ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ የተላከ 09 ገጽ
2. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብሄራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት በቁጥር ደመ42/48/08 በ23/9/08 ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ የታክቲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት የተላከ በፀረ ሽብርተኝነት አንቀጽ 652/2001 አንቀጽ 23/1/ የተዘጋጀ የመረጃ ሪፖርት 04 ገጽ
3. ከ1ኛ ተከሳሽ በማህበራዊ ድረገጽ አማካኝነት በኦሮሚያ ክልል የሚገኙና ከተሞችና ወረዳ ከተለያዩ ግለሰቦች ጋር ሲያደርጋቸው የነበሩ እንቅስቃሴዎች የሚገልፁ የመልዕክት ልውውጦች በ20/5/08 ዓ.ም ታዛቢዎች በተገኑበት የወጣ .......... ገጽ



ETHIOPIA HUMAN RIGHTS PROJECT

4. በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ቡራዩ ከተማ ስለደረሰው የንብረት ጉዳት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ በቀን 21/04/08 ዓ.ም ለቡራዩ ከተማ አስተዳደር በኦሮሚያ የተፃፈ ከነ አማርኛ ትርጉም 13 ገጽ

5. 3ኛ ተከሳሽ የኦነግ ባንዲራና የተለያየ የቅስቀሳ ፅሁፎች ከሞባይል ሁዋዊ ሞባይል ሞዴል ቁጥርY 630–UOSL መለያ ቁጥር I 3 PBY 1531000010б ውስጥ የተገኘ ስለመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ በፎረንሲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት ተመርምሮ ስለመረጋገጡ በቀን 7/7/08 ዓ.ም የተፃፈ ...... ገጽ

6. ከ1ኛ ተከሳሽ የኦነግ ባንዲራ ስለመገኘቱ የብርበራ ቃለ ጉባኤ..... ገጽ

<u>ሐ/ ኤግዚቢት</u>

1. ከ1ኛ ተከሳሽ የኦነግ አርማ ስለመገኘቱ በፖሊስ የኤግዚቢት መዝገብ ቁጥር 238/08 ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

2. ከ1ኛ ተከሳሽ የተገኘ ሞባይል በኤግዚቢት መዝገብ ቁጥር 232/08 እና በ235/08 በፖሊስ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

3. ከ3ኛ ተከሳሽ የተያዘ ሁዋዊ የሞባይል በኢ/መ/ቱ በፌዴራል ፖሊስ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex --------------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia


ETHIOPIA HUMAN RIGHTS PROJECT